# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዛአደር፣ገበሬ፣ነጋዴ፣ወታደር፣ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም።

ቁጥር 32 ቀን 25/3/68

## አብዮት ቀልባሾች ሲተባበሩ

በማንኛውም ህዝብ አብዮት ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ግለትና መብረድ መፈራረቃቸውን ታሪክ ያስተምረናል።አብዮት ትግል እንደመሆኑ አብዮተኛ ሃይሎች ገፍተው አድሃሪ ሃይሎችን ሲጥሉ አብዮቱ ይራመዳል።አድሃሪ ሃይሎች ያላቸውን ሃይል አስተባብረው የሙት ሙታቸውን ሲፈራገጡ አብዮቱን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ይቀለብሳሉ።ዛሬ አብዮቱ በዚህ የአድሃሪ ሃይሎች መፈራገጥ አደጋ ላይ ጥሎት ሊቀለበስና እርምጃው ሊዘገይ በሚያሰጋበት ደረጃ ላይ ይገኛል።የጉልተኞች ተስፋ መቁረጥ በተስፋ ማግኘት ሲለወጥ፣ የኢምፔሪያሊዝም ግፊት እየጠነከረ ሲሄድ፣ የደርጉ ፀረ ዲሞክራሲ፣ፀረህዝብና ፀረአብዮት ድርጊቶች እየበዙና እየሰመሩ ሲሄዱ፣ የተራማጅ—መሰል አድር—ባዮች ድንፋታ ትልቅ ውዥንብር ሲፈጥር፣ ቆም ብለን ''ወዴት እንሄዳለን!'' ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን።የዚህ ውዥንብር መፈጠር፣ የዲሞክራሲ መጥፋት፣ የፀረአብዮት ሃይሎች መተባበር የሚያስከትለውን አደጋ በ'ሰፊው ሕዝብ ድምጽ' ቁጥር 31 በአጭሩ ለማመልከት ሞክረናል።ለዚህም አደጋ መኖር ዛሬ ጉልህ ማስረጃዎች አሉ።

በሰሜን ኢትዮጵያ ራሱን ''የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ማህበር'' ብሎ የሚጠራው የነጋ ተገኝ፣የኢያሱ መንገሻና የመንገሻ ስዩም ቡድን እነአድማሴን በቤገምድር፣እነስማ' ነህን በጎጃም፣እነብርሃነ መስቀልን በወሎ ይዞ በደርግ ላይ የጀመረትን ትጥቃዊ ትግል ማቀነባበር ጀምሮአል።ከኤርትራው ነቀናቂ ቀኝ ክንፍና ከትግራይ ነቀናቂዎች ጋር በመተባበር፣ የአፋሩን አሊ ሚራህ ጨምሮ፣ በኢምፔሪያሊዝምና በአድሃሪ የአረብ አገሮች አበረታችነትና ድጋፍ የፊውዳል ስርአትን ለመመለስ ይፈጨራል፤ በሰፊው ህዝብ አብዮታዊ ክንድ ከፍተኛ አደጋ የተጣለበትን ፊውዶ—ቡርዧ አገዛዝ ከማጣጣር ሊያድነውና ነፍስ ሊዘራበት ይሞክራል።

ፀረህዝቡም ደርግ በዲሞክራሲ ሊፈቱ የሚችሉትን ቅራኔዎች በሃይል በመጠቀም ለማጥፋት በህዝብ ላይ ትልቅ እልቂት ያደርጋል።የደርጉ ቀኝ ክንፍ በእሳቱ ላይ ነዳጅ እየጨመረ ህዝቡ እንዲነሳ፣ ከአድሃሪዎች ጋር እንዲሰለፍ፣ በአፋር በጎጃም፣በቤገምድር፣በወሎ አድሃሪዎችን በመሾም፣ አድገት በህብረትን በማጨናገፍ የአብዮቱን ጠላትና ወዳጅ በአንድ ላይ በመምታት ይረዳል።ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ መፍትሄ ያለውን የኤርትራን ህዝቦች_ብሄር ጥያቄ በብሄር ትምክህተኝነትና በፋሽስታዊ አመጽ በሚመራ እልቂት ሊገታው ሲሞክር ይታያል።መለስ ብሎ ደግሞ በቤገምድር፣በሰሜን ሸዋ፣በጎጃም በትግራይ የ'ሰላም መልእክተኞች' ብሎ አብዮቱ እንዲቀለበስ የሚጥሩ ግለሰቦችን ''ሸማግሌ'' እያለ ለሸፍቶች መታረቂያ የሚሆን ሃሳብ እየያዙ እንዲሄዱ ያደርጋል።

በደቡብ ኢትዮጵያ የደርጉ ፀረዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ከፀረህዝቡ ቢሮክራሲያዊ አስተዳደር ጋር እየተመሳጠረ አብዮቱን ለመግታት አገጣጣውን በማስለቀቅ ላይ ይገኛል።ህዝቡ በአጭሩ ደረጃ ያገኛቸው አብዮቱን ሊገፉ የሚችሉ ድሎች በስራ ላይ እንዳይውሉ ለቀንጣት ያህል እንኳን ያልተነካው የአጤ ቢሮክራሲ ከአድሃሪዎች ወገፊት እያመለጡ የሄዱትን መመሪያዎች በየደሴው ይቀብራቸዋል፤ወይም ተጠምዘው እንዲተረጎሙ፣ በስራ ላይ እንዳይውሉ በተለመደው የነገር መጠምጠምና ማራዘም ዘዴው ፍረቢስ ያደርጋቸዋል።ምሳሌ

ቢያስፈልግ የመሬት ይዞታውን አዋጅ ስለ1967 ዓ.ም. ሰበሰ በደርግና በአገር አስተ
ዳደር ሚኒስቴር የወጣው ሰርኩላር እንዴት ሊሽረው እንደሞከረ እውቅ ስለሆነ ጠቀስን
እናልፈዋለን::በየክፍለአገሩ የሚዘዋወሩት የደርግ አባሎችም በሃረርጌ:በሲዳሞ:በወለጋ
...ወዘተ. የገበሬዎችን ማህበራት ስብሰባዎች መበተናቸውን፣ በወላሞ የገበሬ ማህበራት
መሪዎችንና የመሬ ይዞታ ሰራተኞችን ማሰረሸናቸው፣ ማስታወሱ ይበቃል::ማህበሮች በት
እዛዝ የታገዱባቸው እንዲሁ ብዙ በታዎች ሲሆኑ ሸፍተው የነበሩ የህዝብ ጠላቶች በተደ
ናበሩ የደርግ አባላት አስተናባሪነትና በቢሮክራሲው እገናኝነት ከነትጥቃቸው እንዲገቡና
እንዲደራጁ መደረጉ ጉልተው የሚታዩ እውቅ ጉዳዮች ናቸው::ይህም ተግባር እየተስፋፋ
ለመሄዱ አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይበቃል::

በሲዳሞ ክፍለአገር በመስከረምና በጥቅምት ወራት በአሬር አውራጃ:በሃገረማር
ያምና በቡርጂ ወረዳዎች፣ በደራሳ አውራጃ:በአማሮ ኬሉ ፀረዳ ሻለቃ ከተማና ሃምሳ አ
ለቃ ከበደ የተባሉት የደርግ አባሎች ባዘጋጁት ሴራ መሰረት አበራ ሞልቶትና ሻለቃ ታ
ከለ በተባሉት ባለስልጣኖች ቀስቃሽነትና መሪነት የነገሉ በረናን አንድ ሻምበል ጦርና
የአዋሳን ፈጥኖ—ደራሽ ጦር በማሰለፍ በጉጂና በደራሳ ብሄረሰቦች ላይ ከፍተኛ ዘመቻ
በማድረግ ታለቅ እልቂት አድርሰዋል::''ተወናብደው ጫካ የገቡት እጃቸውን ሰጡ፣ ወደ
ህብረተሰቡ ተመለሱ'' እየተባለ የሚለፈፍላቸው የቀድሞ የመሬት ከበርቴዎች ከክፍለአገሩ
ምክትል አስተዳዳሪ ከአበራ ሞልቶትና ከሻለቃ ታከለ ጋር በመተባበር፣ ከየካቲት አንቀ
ስቃሴ በፊት ጀምሮ ''መሬት ላራሹ'' በሚለው መፈክር ስር ይታገል የነበረውን ጭቆን
የሲዳሞ ህዝብ አብዮታዊ እርምጃ ለማደናቀፍ ታለቅ ዘመቻ አድርገዋል፤ ብዙ ህዝብ አስ
ጨርሰዋል::

እነዚህ የደርግ አባላት ከላይ የተጠቀሱትን ሃይሎች አስተባብረው በገንባር
ቀደምነት በዘመቻው ሲባተፉ ''ጉጂ ሸፍቷል'' በሚል ቢሮክራሲው በፈጠረው ሃሰተኛ ም
ክንያት ነበር::በተደረገውም ፀረህዝብ ዘመቻ ሰባት ትላለቅ ቤተሰቦች የሚገኙበትን
አንድ መንደር ከህፃን እስከአበቃ ሸማግሌ ጨፍጭፈው አውደመዋል::በሲዳሞ አብዮታዊ
ትግል በመሪነታቸው የታወቁትን እነኤለሹ በሪያን:እነኤሌማን:እነአዱላ ጉሌሌን:እነርባ
ማናሬን:እነአስፋው ጃራን በሃገረማርያም ከተማ እስር ቤት አስገብተው ረሸነዋቸዋል::
ከገበሬ ማህበራትም ከያንዳንዱ 25 ሰዎች አሰልፈው አንዱን ክፍል ከሌላው ጋር እንዲ
ዋጋ አድርገው ብዙ ተራማጅ ገበሬዎችን ጨርሰዋል::

ወታደሮቹ ከነሻምበላቸው በነጠኞቹ እየተጋበዙና እስከ $ 10000 /አስር
ሺህ ብር/ ድረስ ጥሬ ገንዘብ ከመሬት ከበርቴዎች እየተዋጣ ተሰጥቶአቸው ይህን ሁሉ
እርስአደር ህዝብ ሲጨርሱ ሰናይ በወታደሩ ልዩ ልዩ ክፍሎች:በመንግስቱ ቢሮክራሲ:
በጉልተኞች:በመሳፍንት ርዝራዦችና እንዲሁም በአድሃሪ የደርግ አባላት መካከል አብዮትን
ለመቀልበስ የተገባው ቃልኪዳን በሰፊው ህዝብ ላይ ከፍተኛ አደጋን ሊያስከትል እንደሚ
ችል ከመቸውም ይበልጥ ያረጋግጥልናል::

በሃረርጌ:በገሙጎፋ:በቡታጅራ የደርግ አባሎች ያስገረፏትን:ያስረሸኑትን የገ
በሬ ማህበር መሪ፣ ወይንም ፖሊሶች የሚያባድዱአቸውን ንቁ ገበሬዎች ለመዘርዘር ይህች
ጽሁፍ አትበቃንም::አደጋውን ለመጠቆም ያህል የጠቀስናቸው ምሳሌዎች ይበቃሉ ብለን አ
ንገምታለን::ይልቀስ ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ የሚለውን ጥያቄ
ነው::የታሪክ ፍርጃ ሆኖ መለዩ ለባሹ የንኡስ ከበርቴ መደብ ''የአብዮቱ ገንባር ቀ
ደም ሃይል'' እየተባለ በሚወደሰበት በዛሬው አስቸጋሪ ታሪካዊ ወቀት አብዮቱ እንዴት
ሊገፋ ይችላል? ተራማጅነትን ከአድሃሪነት:አንዳንድ ህዝባዊ ዝንባሌዎችን ከአጠቃላይ
ፀረህዝብነት ጋር አዋህዶ የያዘው፣ ለብሄር ተምክህተኝነቱ ለከት በማጣት በስመአንድነት
የአገሪቱን መገነጣጠል፣ የሰፊውን ህዝብ እርስበርሱ መተላለቅ የሚያዘጋጀው የቀራኒዎች
ተዋህዶ የሆነው ደርግ እስከመቼ የአብዮቱ አንቀፋት ሆኖ ይቀያል?

የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት በየካቲት በፈነዳበት ጊዜና እንደሰደድ እሳት ከዳር
ዳር ተቀጣጥሎ ፍርስርሱ የወጣውን፡የበከተውን፡የተሳውን፡በአጤ ሃይለሥላሴ ቅንጡነት ይ
መራ የነበረውን ስርአት በደረመሰበት ጊዜና በዛሬው ጊዜ የሚታየው የህዝቡ ትግል ቢፋ
ፋምም ቢገፋም ቢገርም አብዮቱ ሊራመድ፡ዳር ሊወጣ አልቻለም፡፡ፊውዳሊዝም ከስልጣን ከ
ርቻ ለጊዜው ቢፈ፣ቅለም አልተደመሰሰም፡፡ኢምፔሪያሊዝምም በጥቂቱ ቢፈራ ቢቸር፡እንዳንዳ
ያውም በያሳት ደረጃ ጉሽም ቢደረገም ተጽእኖው ከአገራችን ጠርሶ አልተወገደም፡፡አሁንም
በቢሮክራሲውና በደርጉ ውስጥ ተሰገስገው የሚገኙት የፊውዳሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ቡች
ሎች አብዮቱን ሲቀለብሱት ይጥራሉ፡፡የደርጉ ወላዋይነትና ፀረዲሞክራሲነት አሁን ከህዝቡ
ጋር ተሰለፍ፣ ወዲያው የትግሉ ማእበል ሲያይል ወደፀረህዝብነት፡ወደፀረአብዮትነት እን
ዲቀለበስ ያደርገዋል፡፡

ህዝቡን እንመራለን፣ ወይም እንደአባባላቸው ''ጠበቃህ እንጂ ነገረፈጅህ አ
ይደለንም'' የሚሉት አድርባይ ንኡስ ከበርቴያቸም የተራማጅነት ለምድ ለብሰው፣ ያልተ
ደራጀውን ህዝብ ከቢሮክራሲውና ከመንግስቱ ሃይል ጋር እያጋጩ፣ ሃይሉን እያዳከሙ ፀረ
አብዮት ድርጊት ይፈጽማሉ፡፡በውጭና በውስጥ እየተደራጁ፣ በአዋጅ ደረጃ የተገኙትን ድ
ሎች ሊቀለብሱ ከሚጥሩት ሃይሎች ጋር በመተባበር፣ ጊዜው የማይፈቅደውን መፈክር በመሰን
ዘር፣ ሃቀኛውን ተራማጅ ለአድሃሪያች በመጠቆም ህዝባዊ ስርአት የሚመጠበትን ጊዜ በአ
ጉል ቸኩልነት የሚያርቁት የእነኝህ ተራማጅ መስሎች መኖርና በአንዳንድ አካባቢም ተደ
ማጭነት ማግኘት የህዝቡ ትግል ጉዳና ምን ያህል ረዥም፡መራራና የተወሳሰበ እንደሆነ
በግልጽ ያሳያል፡፡

የአብዮቱን ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝምን፡ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊ
ዝምን በተደራጀ የህዝብ ሃይል መምታትና መደምሰስ በሚያስፈልግበት በዛሬው ወቅት ሰፊው
ህዝብና እውነተኛው ተራማጅ የተለያዩ ጠላቶችን በአንድ ጊዜ እንዲቋቋም ተገድደአል፡፡
መራራ ትግል ማድረግ ቢኖርበትም ያለማመንታት ከትግሉ እሳት ውስጥ ይገባል፡፡የጠላትን
ሃይል በመለከ በመልኩ፡ደረጃ በደረጃ ይሰባብራል፡፡የሰፊውን ህዝብ ትግል በልዩ ልዩ
ዘዴ፡ከልዩ ልዩ ጉዳና ወደአሳቻ መንገድ ሊመሩት የሚሹ ክፍሎች ሁሉ ስህተታቸውን ቢያ
ርሙና ሌላውንም ከማሳሳት ቢቆጠቡ መልካም ነው፡፡

የአብዮቱን ፋና ከፍ አድርጉ በግንባር ቀደምነት ህዝቡን የሚመራ ሃቀኛና አ
ብዮታዊ ድርጅት ህዝቡ ካላቋቋመ አብዮቱ ዳር እንደማይደርስ ዛሬ ግልጽ ነው፡፡እንደዚህ
አይነቱንም ድርጅት ሰፊው ህዝብ የግድ ይፈጥራል፡፡ሁኔታው ያስገድደዋል፡፡ዛሬ የተቀለ
በሰውም አብዮት በተራማጆች ህብረት /በደርጉ ውስጥ ካሉት ተራማጆችም ጭምር/ እንደገና
ወደመስመሩ እንዲመለስ፣ ፈረን እንዲይዝ ህዝቡ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህ እውነተኛ ተራማጆች፣ በታታኝ አጋፋጮች ባይሆኑ እውነተኛ አብዮተኞችና
የአብዮቱ ደጋፊያች በሙሉ ዛሬ ፀረህዝብ የደርግ አባሎች እየተጋለጡ ለፍርድ እንዲቀርቡ፣
ሰፊው ህዝብ ይደራጅና ይታጠቅ ዘንድ በአዋጅ የተወሰዱት መብቶች እንዲመለሱለት፣ በአ
ብዮታውያን ሃይሎች መካከል ሰፊና ሃቀኛ ወይይት እንዲደረግ፣ የአብዮቱ መስመር እንዲ
ጠራና በፀረአብዮት ሃይሎችም ላይ ለሚደረገው ከፍተኛ ትግል ዝግጅት እንዲፋፋም ''የአ
ስቸኳይ ጊዜ'' አዋጁ እንዲነሳና የታሰሩት ተራማጆች በሙሉ እንዲፈቱ ይጠይቃሉ፣ ይታ
ገላሉም፡፡

በዋነኞቹ የሰፊው ህዝብ ጠላቶች ላይ ሰልፉን ለማባመር ዛሬ ለዲሞክራሲያዊ
መብቶች መታገል ያስፈልጋል፡፡ለነዚህም የሚደረገው ትግል በንኡስ ከበርቴ ምኞት በሚረ
ኩና መስመር በለቀቁ አድርባዮች እንደሚደረገው ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት መስመሩን
በተዛዋዋሪ መንገድ በመከለስ አይደለም፡፡ይህንኑ መስመር አጥብቆ ይዞ በዚሁ የትግል
ጉዳና ላይ የሚያደናቅፉትን ደንቃራዎች ሁሉ በልዩ ልዩ ዘዴ በመታገል ነው፡፡

ዛሬ ከደርግ ጋር የሚደረገው ትግል የሚፋፋመው ዲሞክራሲ አሁን በሚለው መፈክር ስር ነው::መንግስቱ ፀረህዝብ ሃይሎች በሙሉ በህዝቡ ላይ የሚፈጽሙት አሰቃቂ ድርጊት ከዲሞክራሲ መጥፋት የመነጨ መሆኑን ድርጊቶችን እያጋለጡ በማሳየት ነው::የታሰሩ ተራማጅ ምሁራን፡ዘማቾች፡የሰራተኛ ማህበራት መሪዎች፡የገበሬ ማህበራት መሪዎች እንዲፈቱ በማድረግ ነው::ፀረህዝብ ድርጊት የሚፈጽሙት ቢሮክራቶችና ወታደሮች/ከደርግ አባላትም መካከል ሆኑ ከውጭ/ ፍርዳቸውን እንዲያገኙ በመታገል ነው::

በዚህ ወደድርጅት፣ ከዚያም ወደህዝባዊ ትጥቅና ከዚያም ወደህዝባዊ መንግስት እንደርሳለን::የአብዮት ቀለባሾች መተባበር ጊዜያዊ ችግሮችን ቢፈጥርም ከዚህ አላማችን ንቅንቅ አያደርገንም::አጥብቀን እንታገላለን::የመንደር አሉባልታና ቀጥ ያጣ የጥቃ ዘመቻን እናወግዛለን::ገንቢ የሆነ ሃቀኛ ሂስን እንቀበላለን::ከቀኝም ሆነ "ከግራ" ሆነው፣ በስልጣን ኮርቻ ላይ ወጥተውም ሆነ ለዚያ እያሸቃበጡ የሰፊውን ህዝብ የአብዮት ጉዳና የሚያስቱትን፣ የሚያደናቅፉትን ሁሉ እናወግዛለን፣ እንታገላለን::

የሰፊውን ህዝብ አብዮት የሚያዳክሙ ሃይሎች በሙሉ ይውደሙ::
እውነተኛ ተራማጆች የትግል አንድነት ይፍጠሩ፣ ያጠንክሩ::
የአብዮቱ ፋና ለዘለአለም ይብራ::

አቅማችን የተወሰነ በመሆኑ ብዙ ቅጂዎችን አላሰራጨንምና በይዘቱ የምትስማሙ አንባቢያን በሙሉ አንብባችሁ ላላነበቡ ብታስተላልፉ፣ ከተቻለም ጋዜጣው የሚበራከትበትን ዘዴ በየፊናችሁ ብትፈልጉ ለትግላችን ይበጃል::